***Journal of Afroasiatic Languages/Journal of Afroasiatic Languages, History and Culture (JAAL)***

Volume 12, Number 1, 2023

# BOOK REVIEWS

## የመጽሐፍ ዳሰሳ በ*የዘሩት ሲያፈራ* ላይ

አበበ ዘገዬ

ደመቀ ዘነበ። (2011 ዓ.ም)። *የዘሩት ሲያፈራ*። አድዲስ አበባ፣ ቢሹ አሳታሚ። (የገጽ ብዛት፤ 176)።

### መግቢያ

የዘሩት ሲያፈራ በሚል አርእስት የቀረበው የደራሲ ደመቀ ዘነበ መጽሀፍ በደርግ ዘመን የኩባ መንግስት ለኢትዮጵያ ያደረገውን አስተዋኦ የሚመለከት ነው። ይህ መጽሀፍ በዋነኛነት የኩባ መንግስት ለኢትዮጵያ ያደረግውን ድጋፍና በዘመኑ በኩባ የተማሩ ኢትዮጵያውያን የነበራቸውን የሀገር ፍቅር እንዲሁም ወደሀገራቸው ተመልሰው ያደረጉትን አስተዋፆ በስፋት ይገልፃል።

ደራሲው ደመቀ ዘነበ ግለ ታሪካቸው ለትውልድ የሚጠቅም መሆኑን በማመን ተዳፍኖ እንዳይቀር በጽሑፍ ለማስተላለፍ መፈለጋቸውን ይገልፃሉ። የመጽሐፍ ዳሰሳው ዓላማም ይህንኑ እሳቤ ለማጠናከርና አንባቢው ተገቢውን ቁም ነገር እንዲቀስምበት ለማበረታታት ጭምር ነው።

### አጠቃላይ እይታ

የኩባ መንግስት እድሚያቸው ከ9-16 አምት የነበሩ ልጆችን ከኢትዮጵያ በመውስድ እንደ እናት እና አባት ተንከባክቦ አስተምሮ ለቁምነግር ማድረሱ ታሪክ የማይረሳው ውለታ መሆንኑ መጭው ትውልድ እንድረዳ ይህ መፅሀፍ የበኩሉን ሃላፊነት ተወጥቷል ማለት ይቻላል። መጽሀፉ ከታሪክ ማስተወሻነት አልፎ በውጭ የተማረው ወደ ሀገርቤት ተመልሶ በተማረበት ሙያ የሚያደርግው ተሳትፎ ሀገር ለማሳደግ የሚኖረውን ፋይዳ ያሳያል። በውጭ ሀገር ተምሮ ወደ እናት ሀገር ተመልሶ ሀገራዊ ግዴታን መወጣት ከቀድሞ የኩባ ተማሪዎች የምንማረው ትልቅ የዜግነት ግዴታ ነው።

ደራሲው በተወለዱባት የወሎዋ ደሴ ከተማ ከቄስ ትምህርት ፊደል ጥናትና ግብረገብነት አንስቶ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ዘልቀዋል። በመምህርነት ሙያ ተሰማርተውም ሀገራቸውን አገልግለዋል። በኢትዮጵያ ተማሪዎች ትግል ስሙ ጎልቶ ከሚነገርለት የወይዘሮ ስሂን ትምህርት ቤት ካፈራቸው ተማሪዎች አንዱ ናቸው። በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ተከታትለው አጠናቀዋል። ቀጥለውም በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህር ሆነው አስተምረዋል። በወቅቱ በተካሄደው የሥርዓት ለውጥ ምክንያት ሥራቸውን ለመልቀቅ ጫና እንደነበረባቸው ይገልጻሉ። ሆኖም በወቅቱ የኩባ መንግሥት ባመቻቸው እድል ወደ ኩባ ሄደው እንዲማሩ የተመለመሉትን አንድ ሺ ሁለት መቶ ተማሪዎች ይዘው በሚወዱት የማስተማር ሙያ እንዲሳተፉ ከደርግ መንግስት ጥሪ ይቀርብላቸዋል። ጥሪውንም ተቀብለው ከሌሎች ባልደረቦቻቸው ጋር ወደ ኩባ አቅንተዋል። ደራሲው በኩባ ስለነበሩ ተማሪዎችና መምህራን ማኅበራዊ ትስስርና ውጣ ውረድ፣ በሱማሊያ ወረራ ወቅት መስዋእትነት ስለከፈሉት የኩባ ወታደሮች ያልተቆጠበ ውለታ በሰፊው ያልተነገረው ታሪክ እንዲሁም የሕይወት ልምዳቸውን በመጽሐፋቸው አካፍለዋል። መፅሀፉ በዋናነት ደራሲው በመምህርነት ሙያ ኩባ ሀገር በነበሩበት ወቅት በሥራ ስለነበራቸው ተሳትፎ፣ ስለ ኢትዮጵያውያን የኩባ ተማሪዎች፣ ስለ ኢትዮ-ኩባ ዲፕሎማሲዊ ወዳጅነትና ወታደራዊ ድጋፍ ውለታ ይተነትናል።

መጽሐፉ ጦርነት፣ ስደት፣ ረሀብና ኋላቀርነት በሀገር ኢኮኖሚ ያስከተለው ተጽዕኖ በውጭ ሀገራት ወዳጅ ፍለጋ ያስገድድ እንደነበርና የኩባ ወዳጅነትና እርዳታም የዚሁ አካል መሆኑን ያስረዳል። በቀላል አማርኛ መቅረቡና በርካታ ተዛማጅ የፎቶግራፍ ማስረጃዎች የተደገፈ መሆኑ የመጽሐፉ ጠንካራ ጎኖች ተደርገው ሊወሰዱ ይችላል። እንዳዚህ መቅረቡ በማናቸውም እድሜ ደረጃ ለሚገኝ አንባቢ ተስማሚ አድርጎታል። በተጨማሪም የተጠቀሙት ዋቢ መጽሓፍት ሳቢና ከርዕሱ ጭብጥ ጋር የተጣጣሙ ናቸው።

## የመፅሀፉ አደረጃጀት

መጽሐፉ በ17 አነስተኛ ምእራፎች የተከፋፈለ የሕይወት ዘመን ትዝታ ላይ የሚያጠነጥን ግለ ታሪክ (ማስታወሻ) ነው።

ምዕራፍ አንድ ከኢትዮጵያ ቀደምት ታሪክ ሥልጣኔ ታላቅነት ባሻገር በየጊዜው የተካሄዱ አሰልች ጦርነቶች ለአስከፊ ድህነትና ኋላቀርነት መጋለጥ ምክንያት መሆናቸውን ይገልፃል። ይህ ምዕራፍ በሶማሊያው ሰይድ ባሬ የእብሪት ወረራ ወቅት የኩባ ወታደራዊ ድጋፍንም በአጭሩ ያትታል። ምዕራፍ ሁለት ስለ ኩባ እና ሕዝቧ ታሪክ፣ ባሕል፣ የአኗኗር ዘይቤ፣ ኢኮኖሚ እንዲሁም ቀደም ሲል ከስፔን አፓርታይድ ቅኝ አገዛዝ ለመላቀቅ እ.ኤ.አ በ1898 ዓ.ም የተደረገው የነጻነት ትግል ሂደት ወደ ብሔርተኝነት መሸጋገሩ ያስገኘው ውጤት፣ ከአሜሪካ አፍንጫ ስር ስለተወለደው የኩባ አብዮተኞችና የነጻነት ታጋዮች ሆ ማርቲ፣ ፊደል ካስትሮ እና ቼ ጉቬራ ዓይነተኛ ሚና በሰፊው ይተርካል። ምዕራፍ ሦስት የኢትዮጵያ እና ኩባ ወዳጅነት፣ የባሕል ትስስር መጠናከሩ

በተለይም አምባሳደር ካሳ ከበደ የሕጻናትና ጀግኖች አምባ በመልካም እሴት እንዲደራጅ በማድረግ በሱማሊያ ወረራ ምክንያት ወላጆቻቸውን ያጡ ሕጻናት ወደ ማሳደጊya አምባው እንዲገቡና በኋላም ተመልምለው ወደ ኩባ ጭምር እንደተላኩ የነበራቸውን ጉልኅ አስተዋጽዖ ዘርዘር አድረጎ ያስረዳል። ከምዕራፍ አራት እስከ ስምንት ያለው የመጽሐፉ ይዘት በአጠቃላይ ወደ ኩባ ሀገር ለትምህርት የተላኩ ወጣት ተማሪዎች እና መምህራኖቻቸው የጉዞ ሁኔታ፣ ውጣ ውረድና ገጠመኞች፣ የኩባውን የሥራ ባሕል እንዲሁም ከሌሎች ሀገራት ተማሪዎች ጋር መስተጋብር ምን እንደሚመስል በደምሳሳው የተመላከተበት ነው። ምዕራፍ ዘጠኝ እና አስር በኩባ ለኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ስለ መደበኛ ትምህርት አሰጣጥ፣ የትምህር ቤቶቹ ሥነ ሥርዓት፣ ንድፈ ሃሳብ፣ የሙያ ክህሎት፣ የሰውነት ማጎልመሻ፣ የእርሻ ትምህርት፣ ሁለገብ እውቀት፣ ወታደራዊ ስልጠና፣ ባሕልና ስፖርት ነክ እንቅስቃሴ ተሳትፎን ለሀገራችን የሚኖረውን ፋይዳ ያስረዳል። ምዕራፍ አስራ አንድ ደግሞ በምዕራፍ ዘጠኝ ከተብራራው ስፖርትና የባሕል ነክ እንቅስቃሴ ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ይስተዋላል። ምዕራፍ አስራ ሁለት እና አስራ ሦስት በኩባ ተማሪዎች እና መምህራን ቀይታ በማኅበራዊ ግንኙነት ረገድ ያጋጠማቸው ያለመግባባት ውዝግቦችን በተለይም የቡድን መሪ የነበሩትን ኮሎኔል አሰፋ በርሔ ጊላይን የአያያዝ ድክመት እንዲሁም ችግሮች እንዲስተካከሉ ለአምባሳደሩና ለፐሬዝዳንት መንግስቱ በማሳወቅ ጭምር የተወሰዱ እርምጃዎችን በተመለከተ ያብራራል። ምዕራፍ አስራ አራት እና አስራ አምስት የፕሬዝዳንት መንግስቱ በኩባ ያልተጠበቀ ጉብኝት በተማሪዎች እና መምህራን ሠራተኞች መካከል ጤናማ ግንኙነት እንዲኖርና ችግሮች እንዳይቀጥሉ ስለማገዙ እንዲሁም መምህራኖቹ ተማሪዎችን እንደወላጅ ሆነው በማነጽና በመንከባከብ ተሰጥኦዋቸውን እንዲያጎለብቱ ያበረከቱትን ጉልህ አስተዋጽዖ እውቅና አሰጣጥ ሁኔታ በሰፊው ይገልጻል።

ምዕራፍ አስራ ስድስት የቤተሰብ ሕይዎት በተመለከተ እንዲሁም የኩባ ተማሪዎች የተዋጣላቸው ስፔሺሊስት ሀኪም ሆነው በኢትዮጵያ ዝነኛ ሆስፒታሎች እያበረከቱት ስላለው ድርሻ በምሳሌነት ጥቂቶቹን (እነ ዶክተር ሙሉዓለም ገሠሠ፣ ዶክተር መብራቱ ጀምበሬ፣ ዶክተር ሸዋዓለም ነጋሽ፣ ዶክተር ስዩም ካሳ፣ ዶክተር ዓለማዬሁ ተገኝ የመሳሰሉትን) ጠቅሶ ቀደም ሲል ሲነዛ የነበረውን የትምህርት ጥራት ችግር አሉባልታና ገጽታ ለመቀየር ይሞግታል።[1] የመጨረሻው ምዕራፍ አስራ ሰባት የመጽሐፉ ማገባደጃ ዋና ፍሬ ሃሳቡ ተጨምቆ የቀረበበትት ነው።

መፅሀፉ በአጠቃላይ የኩባ መንግስት ለኢትዮጵያ የዋለው ዘርፈ ብዙ ውለታ ይዘክራል። በኩባ የትምህርት እድል አማካኝነት በልዩ ልዩ ሙያዎች የሰለጠኑ ኢትዮጵያውን ወጣቶች ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ለማገልገል ቢፈልጉም ለምስራቁ የሶሺያሊስት ርዕዮተ ዓለም በነበረ የተዛባ አመለካከት የተነሳ ሥራ ሳይመደቡ መጉላላት

1 በመጽሐፉ በገጽ 168 ላይ የቀ.ኃ.ሥ የቤተ ዛታ ሆስፒታል ተብሎ የተጠቀሰው በአርትኦት ክፍተት ምክንያት ሲሆን የቀ.ኃ.ሥ ቤተሳይዳ ሆስፒታል የአሁኑ የካቲት 12 ሆስፒታል በሚል ታሪኩን አንባቢ እግረ መንገዱን ቢገነዘበው መልካም ይሆናል።

ያጋጥማቸው ነበር። ይሁን እንጂ ያንን አልፈው ለሀገራቸው በርካት አስተዋፆ አድርገዋል። ደራሲው የኩባ ተማሪውች በሀገር ፍቅር ሚዛን ያደርጉትን አስተዋፅኦ ለሌሎች አርአያ እንደሚሆን በልበሙሉነት ይገልጻል። ለኩባ ተማሪዎች አሉታዊ እይታ ሊፈጠር የቻለው ሀገራችን በሰሜኑ የጸረ-ተገንጣይ ጦርነት ላይ በነበረችበት ወቅት የሀኪሞች እጥረት በማጋጠሙ ትምህርታቸውን ሳያጠናቅቁ ከኩባ በመጡ ተማሪዎች በተፈጠረ የህክምና ስህተት ምክንያት መሆኑን ጸሀፊው በጽሁፋቸው አልሸሸጉም።

## መደምደሚያ

የደራሲ ደመቀ ዘነበ አበርክቶት ይህን መፅሀፍ ለአንባቢ በማቅረቡ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። መፅሀፉ በኢትዮጵያ እና ኩባ መካከል የነበረውን ጠንካራ ዲፕሎሲዊ ወዳጅነት በተለይም ኩባውያን በሶማሊያ ወረራ ወቅት እስከ ሕይወት መስዋዕትነት መክፈላቸው፣ የትምህርት እድል ለኢትዮጵያውያን መመቻቸትና ተማሪዎቹም ተመልሰው ሀገራቸውን ለማገልገል ያሳዩት ፍላጎት እና ሌሎችንም ዝርዝር ጉዳዮች ጠቃሚ መረጃ ይሰጣል። መጽሐፉ ብዙ ያልተነገረላቸው እውቅ ስፔሽያሊስት የቀዶ ጥገና ሀኪሞች የኩባ ተማሪዎች አባል መሆናቸው ይገልፅል። በአጠቃላይ የኩባን ያልተቆጠበ ውለታ የታሪክ አሻራ በአግባቡ ጎላ ብሎ ያልተነገረ መሆኑ የፈጠረባቸው ቁጭት ሌሎች ባልደረቦቻቸው በጽሑፍ ሳያስተላለፉ ማለፍ የሚፈጥረውን ስሜት ታሳቢ ማድረጋቸው ተገቢ ነው። ይህ የግለ ታሪክ ማስታወሻ በሁለቱ ሀገራት ያጠነጠነ ቢሆንም ለኢትዮጵያ ታሪክ አጠናን የሚኖረው ድርሻ ቀላላ አይደለም። በተጨማሪም ይህ በኩባ የተማሩ ድንቅ ኢትዮጵያዊያኖች ተግባር ለአሁኑ የኢትዮያዊያን ፍልሰት የሚያስተምረው ትልቅም ነገር አለ። ከደርግ ውድቀት በኋላ በዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ ያሉ ዜጎችን ጨምሮ ብዙ ኢትዮጵያኖች ወደ አሜሪካ፤ አውሮፓ፤ መካከለኛው ምስራቅ እና ደብቡ አፍሪካ ፈልሰዋል። እነዚህ ኢትዮጵያዊያን በዚህ መጽሃፍ ከተገለጸው የቀድሞ የኩባ ተማሪዎች ሀገር ወዳድነት እና ወደ እናት ሀገራቸው ተመልሰው ያበረከቱትን አስተዋፅኦ አርአያ ቢያደርጉ ለትውልድ ሀገራቸው የሚኖረው ፋይዳ ብዙ ነው።